# ኢትዮጵያ: ሕዝባዊ ተቃውሞና የወታደራዊ መንግሥት ጥያቄ

እስክንድር ነጋ:-  -  በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደፃፈው
<u>አዲስ አበባ</u>

የአማርኛ ትርጉም:- -  የኢትዮጵያ ዛሬ ዝግጅት ክፍል

የደርባባውና የ82 ዓመቱ አዛውንት ሆስኒ ሙባረክ ከስልጣን መውረድ ዓርብ አመሻሽ ላይ ሲበሰር፣ በግብፅ ታሪክ ተሰምቶ የማይታወቅ እልልታና ሆታ ቀለጠ... ሕዝብ በደስታ ሰክሮ ሌሊቱን አሳለፈ.....

አይ ካይሮ ያቺን ምሽት!... እንዴት ተረሳለች?... እኛስ አብረናቸው አላደርንም እንዴ?... ዕድሜ ለአልጀዚራ፣ ለቢ.ቢ.ሲ፣ ለሲ.ኤን.ኤን፣ ለፕሬስ ቲቪ... የካይሮ ሕፃናት እንዴት ይረሱናል?... ገብቷቸው ይሆን እንዲያ የፈነጠዙት?... ጨለማውን ብርሃን እንደዋጠው እውን ለእነሱም ታይቷቸው ነበርን?... ቀልባቸው ነግሯቸው ይሆን?... የትላልቆቹማ ምኑ ይወራል... በእነሱ ደስታ እኛም እምባ ተራጭተናል...

ቆም ብሎ ለማሰብ አፍታ የተገኘው በነጋታው ነበር፤ ዕለተ ቅዳሜ::

ለመሆኑ፣ አዲሶቹ የግብፅ መሪዎች ከቶ እነማን ይሁኑ? የሕዝቡን የዲሞክራሲ ተስፋ አክብረው ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉስ ናቸውን?

መቼስ፣ ብዙ ሚሊዮን ሕዝብ ወጥ መልስ ይኖረዋል ተብሎ አይጠበቅም:: ያ እንደ አንድ ቤተሰብ ተመሳጥሮ ሙባረክን ያንበረከከ ሕዝብ ግን፣ የቅዳሜ ጀምበር ገና ሳትጠልቅ ስሜቱ ተደበላልቆ አረፈው:: የሚያስገርም ፍጥነት:: ይባስ ብሎ፣ የሕዝባዊው ተቃውሞ እምብርት በነበረችው ታሂር አደባባይ ጎራ ለይቶ በመፈክር መፋለም ጀመረ::

«ወደቤት የመመለሻው ጊዜ አሁን ነው» በማለት በሺህዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች አደባባዩን አደበላለቁት፤ ጓዛቸውን እየጠቀለሉ:: አዲሱ የግብፅ መንግሥት፣ ሕዝቡ ለ18 ቀናት ከትሞ ከሰነባበተበት ታሂር አደባባይ እንዲለቅ አዎንታዊ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል የሚሉት መሆናቸው ነው::

«አብዮቱን ከግብ ሳናደርስ አንነቃነቅም» የሚል የሺህዎች የተቃውሞ ጩኸት ወዲያው ተቀበላቸው:: «የሕዝብ ራዕይ ከሙባረክ ስንብት በእጅጉ የመጠቀ ፋይዳ ያለው ነው» ብለው ተከራከሩ፤ አደባባዩን ለቆ ለመሄድ ግዜው አልደረሰም በማለት::

የውዝግባቸውን ምንጭ ላስተዋውቅዎ::

«Egyptian Military Council» ተብሎ ይጠራል፤ በእንግሊዝኛው:: «የግብፅ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ» እንደማለት ነው በአማርኛ ፍቺው:: አዎ! ደርግ! ታዲያ ይሄ አያስደነግጥም? (ደርግ የግዕዝ ቃል ሲሆን፣ በእንግሊዝኛው «Committee» ወይም «Council» ማለት ነው::)

ነገሩ ከዚህም ይብሳል:: ወታደራዊው ምክር ቤት 6 አባላት አሉት:: ሁሉም የሙባረክ ተሿሚዎች ናቸው:: ፊልድ ማርሻል መሐመድ ሁሴን ታንታዊ፣ የመከላከያ ሚኒስቴር፣ ሌተና ጄኔራል ሳሚ ሀፌዝ ኢናን፣ የኢታማዦር ሹም፤ ም/ል አድሚራል ሞሐብ ማማሽ፣ የባሕር ኃይል አዛዥ፤ ኤር ማርሻል ራዳ መሐመድ ሀፌዝ ሞሐሜ፣ የአየር ኃይል አዛዥ እና ሌተና ጄኔራል አብዱል አዚዝ ሰይፈዲን፣ የአየር መከላከያ አዛዥ ናቸው የደርጉ አባላት::

የወታደራዊው መንግሥት መሪ ሆነው ብቅ ያሉት ታንታዊ፣ ጀማል አብዱል ናስር ስልጣን ላይ በነበሩበት በ1950ዎቹ አጋማሽ በሶቪየቶች የሰለጠኑ ሰው ናቸው:: ዕድላቸው ሆኖ፣ ገና በተመረቁ ማግስት፣ እ.ኤ.አ በ1956 ዓ.ም፣ ሀገራቸው ባልታሰበ ጦርነት ተናጠች:: ይህ ጦርነት፣ እ.ኤ.አ ከ1940ዎቹ መጨረሻ እስከ 1970ዎቹ መጀመሪያ በነበሩት ዓመታት በግብፅና በእስራኤል መካከል ከተካሄዱት አራት ጦርነቶች ሁለተኛው መሆኑ ነው:: በምክትል መቶ አለቅነት በተሳተፉበት በዚህ ጦርነትም ሆነ በ1967 እና በ1973 (አሁንም እንደ እ.ኤ.አ) በተካሄዱት ቀጣይ ጦርነቶች፣ ታንታዊ የተለየ ክብርና አድናቆት የሚያስጣቸው የጦር ሜዳ ጀብዱ አልፈፀሙም:: ለሶስት አስርተ ዓመታት በዘለቀው የሙባረክ የአገዛዝ ዘመን፣ ለሃያ ዓመታት በመከላከያ ሚኒስቴርነት ተደላድለው እንዲቆዩ ያበቃቸው ዓይነተኛው ምክንያት ይህ እንደሆነ ብዙዎች ይገምታሉ፤ የ«አርቆ አስተዋዩን» ሙባረክ ብልጠት ግምት ውስጥ አስገብተው ማለት ነው::

በ2008 ዓ.ም፣ በግብፅ ያለው የአሜሪካ ኤምባሲ ታንታዊን በተመለከተ ለዋሽንግተን ያስተላለፈውን ሚስጢራዊ ሪፖርት በቅርቡ ዊክሊክስ ይፋ አድርጎታል:: ሪፖርቱ፣ የመከላከያ ሚኒስትሩ ታንታዊ ትኩረት የሙባረክ መንግሥት ተረጋግቶ እንዲያዘግም መሆኑን ሲገልፅ «የለውጥ ፍላጎቱም ሆነ አቅሙም የሌለው ሰው ነው» በማለት አጣጥሏቸዋል::

የታንታዊ ወግ አጥባቂነት ተጨማሪ ማስረጃ ካስፈለገውም፣ ወታደራዊው መንግስት በአብዮቱ ማግስት ባወጣው የፅሁፍ መግለጫ ላይም ተንፀባርቋል:: ሙባረክ «ለሕዝብ ደህንነት ሲሉ» ነው ስልጣናቸውን የለቀቁት በማለት ተንቆለጳጵሰዋል:: በካይሮ ጎዳናዎች ላይ በባዶ እጁ ታሪክ ለሰራው የግብፅ ወጣት እንቆቅልሽ ነው የሆነበት:: ጄኔራሎቹ የትኛውን የታሪክ መዛግብት ነው የሚያጣቅሱት?

ታዲያ፣ ይህ ሁሉ የሚያመላክተው ምንን ነው?

በአሸናፊነት መንፈስ የተጨፈረበት «የሕዝብ ድል» ባዶ ተስፋ መሆኑን ይሆን? እንደ 66ቱ የኢትዮጵያ አብዮት፣ የሕዝብ ድል በጥቂት ወታደሮች ተነጥቋል ብለን መደምደም ይገባን ይሆን? ወይስ የግብፅ አብዮት በመንታ መንገድ ላይ ቆሟል ማለቱ ይበቃል?

ከሁሉ በላይ ደግሞ፣ አንዳንድ የኢሕአዴግ ሹማምንት በለበጣ እንደሚያነበንቡት፣ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ተቃውሞ ቢቀጣጠል፣ እውን ውጤቱ የወታደራዊ አገዛዝ አኪራ ከመሆን አያልፍምን? ከንቱ ልፋት ነው የሚሆነው?

መለስ ላድርግዎት፤ ወደ ግብፅ:: ወታደራዊው መንግሥት የወሰዳቸውን ቀዳማይ እርምጃዎች ልብ ይበሏቸው:-

1. ሕዝቡ በስፋት ሲሳለቅበት የኖረውን ፓርላማ በቅፅበት አፍርሶታል:: (ገዢው ፓርቲ ከ90 በመቶ በላይ መቀመጫዎችን «አሸንፎ» የያዘበት ም/ቤት ነበር::)

2. ሕገ-መንግሥቱን አግዷል::

3. ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ ፈቅዷል::

ጄኔራሎቹ ሙባረክን በቃላት ያሞኳሿሿቸው እንጂ፣ በተግባር ግን፣ የአምባገነንነታቸው ሁለት ዋና ዋና ምሰሶዎችን ለመነቃቀል ቅንጣት ታህል አላመነቱም:: የለውጡን ፍጥነት ለመግታትም ሆነ አቅጣጫውን ፈር ለማሳት አልሞከሩም::

በአንፃሩ፣ የኢትዮጵያው ደርግ፣ አፄ ኃይለሥላሴን ከስልጣን ያወረደ ዕለት ነበረ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑን ነጋሪት አስጎሽሞ ያወጀው::

አማራጭ የፖለቲካ ድርጅቶች ባልነበሩባት ኢትዮጵያ፣ ደርግ ጥርት ያለና ግልፅ ዓላማ ተከስቶለታል:: ግዜ ያለፈበትን የጭሰኛው ስርዓት የማፈራረሱ ተግባር የታሪክ ዕዳው እንደነበር ቁልጭ ብሎ ታይቶታል:: ይህ ደግሞ፣ ኃይልን ተገን አድርጎም ቢሆን ስልጣን ላይ የመቆየት ፅኑ ፍላጎት ጭሮበታል::

የዛሬዋ ግብፅ ግን፣ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች በህቡዕም በይፋም የሚተረማመሱባት ሀገር ናት:: የግብፅ ወታደራዊ መሪዎች የፖለቲካ መድረኩን ብቻቸውን አልተቆጣጠሩትም፤ የመንግሥት ስልጣን እጃቸው ላይ ቢወድቅም:: በሶስት አቅጣጫ ተወጥረዋል:: የዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ አለ፣ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ፣ በተለይ በተለይ ግን፣ ሕዝባዊ ተቃውሞውን ያስተባበሩት ወጣቶች ያቋቋሙት «የአደራ ጠባቂ ምክር ቤት» ክትትል አለባቸው::

የጠራ ዓላማ ያለው ወጣቶቹ አብዮተኞች ጋር ነው እንጂ አዛውንቶቹ የጦር ጄኔራሎች ዘንድ አይደለም:: እንደደርግ፣ ሊፈርስ የሚገባው ስር የሰደደ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚና ፖለቲካ ስርዓት ፊት ለፊታቸው ተጋርጦ አይገኝም:: አንድን ግለሰብ ማዕከል ያደረገ የፖለቲካ ሥርዓት ፍርስራሽ ነው የተረከቡት:: አምባገነናዊው ሥርዓት በሕብረተሰቡ ላይ የተለበጠ ነው:: ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥልቀት የለውም:: መቀረፍ ብቻ ነው የሚሻው::

ግልፅ የሆነ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግቦች ባልተቀመጡበት ሁኔታ ደግሞ፣ ወታደሩ የፖለቲካ ኃይል ሆኖ የመውጣቱ ዕድል እጅግ አነስተኛ ነው፤ በግብፅም ሆነ በኢትዮጵያ::

የግብፅ የዲሞክራሲ አብዮት የመቀልበስ አደጋ አልተጋረጠበትም:: ወታደራዊው መንግሥት ለዲሞክራሲያዊው አብዮት መሰረታዊ ግቦች የተሻለ አማራጭ አለኝ ማለት እስካልተቻለ ድረስ፣ ሊያስነሳው የሚችለው አደጋ ሊኖር አይችልም:: ዓለም በሁለት ተፎካካሪ የኃያላን መንግሥታት ጎራ ተከፋፍላ በምትናጥበት ዘመን የምንኖር ቢሆን ኖሮ፣ የግብፅ ጄኔራሎች አማራጮች በነበራቸው:: ዛሬ ግን አንዱ ጎራ ከስሟል፤ አማራጭ የለም:: በምዕራቡ ዓለም የሚታወቀው ዲሞክራሲ ብቸኛው መንገድ ሆኗል፤ ሕዝቡም ተቀብሎታል:: መፈናፈኛ የለም::

ብልሆቹ የግብፅ ጄኔራሎች ከዚህ ነባራዊ እውነታ ጋር ተስተካክለው መጓዝን መርጠዋል:: ብስለታቸው፣ የረዥም ዘመን ልምዳቸው፣ ክህሎታቸውና ሕዝባዊነታቸው ጎልቶ ይታያል::

እኔ በበኩሌ፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች ከግብፅ ወታደሮች የደበዘዘ ብስለት፣ ልምድ፣ ክህሎትና ሕዝባዊነት አላቸው ብዬ አላምንም:: እንዲያውም፣ የኢትዮጵያ ጄኔራሎች ለሕዝብ መብት ብለው

ወጣትነታቸውን በዱር በገደሉ ያቃጠሉ ናቸው። ሕዝባዊነታቸው ቢልቅ እንጂ ፈፅሞ የሚያንስ አይደለም። ከግብፅ ጄኔራሎች በላይ የሚፈሩበት ምክንያት አይታየኝም። ከመርህ አኳያ፣ ለለበጣው በቂ ምክንያት አላገኘኹለትም።

ወታደር ስልጣን ይውረስ እያልኹኝ አይደለኹም። ይሄ ግልፅ እንዲሆንልኝ እፈልጋለኹ። የሀገሬ የዲሞክራሲ ሽግግር በዚህ መንገድ እንዳይሄድ ነው ምኞቴ፤ ፀሎቴም።

ነገሮች በዚህ አቅጣጫ የግድ ከሄዱ ግን፣ አልደነግጥም።

ደርግ የተዋቀረው ከፍተኛ መኮንኖችን በማግለል ነበር። ከሻለቃ በላይ ያሉትን አላቀፈም። ይህ ክፍተት፤ ለጭፍን ስህተቶቹና መቅሰፍታዊ ፍፃሜው ምክንያት ሆኗል። ከዚህ የቅርብ ጊዜ ታሪክ አኳያ፤ የኢትዮጵያ ወታደሮች ይህንን ስህተት ይደግማሉ ብዬ ለመገመት እቸገራለኹ።

በጄኔራሎች የሚመራ ወታደራዊ መንግሥት፣ ያልተገራ ሳይሆን የሰከነ፣ ከጭፍን አክራሪ ይልቅ ወግ አጥባቂ ነው የሚሆነው። በፖርቱጋል፣ በግሪክ፣ በስፓኝ፣ በናይጄሪያ እንደዚህ ዓይነቶቹ ወታደራዊ መንግሥታት ሀገራቸውን ለተሟላ ዲሞክራሲ ስርዓት አብቅተዋል። ግብፅ በዚያ መንገድ ላይ ነች። በአስደናቂ ፍጥነት አዲስ ሕገ-መንግት በሕዝበ ውሳኔ ፀድቋል። ሙባረክ ከወደቁ ግን፣ ገና ሁለት ወራት እንኳን አልተቆጠሩም። የፖለቲካ ድርጅቶች (የሙባረክ ፓርቲን ጨምሮ) ለምርጫ እየተዘጋጁ ነው። የተዋጣለት የዲሞክራሲ ሽግግር እየሆነ ነው።

ከሁሉም በላይ ግን፣ በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ሀገሮች፣ ወታደሮች እንኳንስ ስልጣንን በብቸኝነት ለመያዝ ቀርቶ፣ ረዘም ላለ ጊዜ በፖለቲካው መድረክ ላይ ለመቆየት የሚያስችል አንዳችም ሰበብ የላቸውም። ዘላቂ ወታደራዊ መንግሥት የሚመሰረትበት የተቀናጀ ርዕዮታዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ መሰረት ፈፅሞ የለም። ዓለም ተለውጣለች።

የትም ይሁን የት፣ ወታደሮች ሊመሩት የሚችሉት አጭር ዕድሜ ያለው የሽግግር መንግሥትን ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ወታደሮች ከዚህ ዓለም አቀፋዊ ድባብ ውጭ አይደሉም። ለመሆን የሚፈልጉበት ምክንያትም አይታየኝም።